# የኤርትራውያንን ንብረት ለመመለስ የወጣው መመሪያና ከበስተጀርባው ያሉ የፖለቲካል ኢኮኖሚ እሳቤዎች

ከዛዲግ አብርሃ

በቅርቡ የኤርትራውያንን ንብረት መመለስን የሚመለከት መመሪያ መውጣቱን በጉዳዩ ላይ የሚዲያ ተቋማት የተለያዩ ትችቶችን በማስተናገድ ላይ ይገኛሉ። በዚህ ረገድ የመመሪያውን መውጣት አስመልክቶ ሚንፀባረቁት አስተያየቶች በሁለት ሊካተቱ የሚችሉ ናቸው። የመጀመሪያው የመመሪያውን መውጣት የሚደግፈውንና አብዛኛውን የኅብረተሰብ ክፍል አቋም የሚያንፀባርቀው አስተያየት ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ በጥቂቶች ተቃዋሚ የፖለቲካ አመራሮች የሚራመደው አስተያየት ግን የደንቡን መውጣት ከአንዳች 'ድብቅ' ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ግብ ጋር በቀጥታ በማገናኘት በሚቀርቡት ተቃውሞዎች የሚወከለው አቋም ነው።

በኋለኛው ውስጥ በተቃውሞ ከሚንፀባረቁት ሃሳቦች ዋነኞቹ የሚያጠነጥኑት ጉዳዩ ቀደም ሲል አከራካሪ የነበረ መሆኑን፣ የኤርትራና የኢትዮጵያን ግንኙነት ያደፈረሰው ጦርነት አቁሟል በማይባልበት ሁኔታ የኤርትራውያኑ መመለስ ብሔራዊ ደህንነትን ለአደጋ የሚያጋልጥ መሆኑን በመጥቀስ መመሪያው ላይ የሰፈሩ የጥንቃቄ ድንጋጌዎችም እንኳ አደጋውን ማስቀረት አይችሉም የሚል አቋም ላይ የተመሰረተ ነው። በተመሳሳይም ይህን አቋም የያዙ ወገኖች የመመሪያው መውጣት ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የስራ አጥ ቁጥር ያባብሳል በማለትም አጥብቀው ይከራከራሉ።

መመሪያውን በመቃወም የሚቀርቡት እነዚህ ክርክሮች መሬት ላይ ያለውን ሀቅ እና እንዲሁም በመመሪያው ሳቢያ ሊከተል የሚችለውን ተጨባጭ አዎንታዊ ውጤት ለመቀበል ካለመሻት የመነጩ የተሳሳቱ አስተያየቶች በመሆናቸው ተፅእኖውን አይወክሉም። ይህን የምልበትን ምክንያትም እንደሚከተለው ለማሳየት እሞክራለሁ።

## 1. እውን ኤርትራዊያን የደህነነት ስጋት መሆን ይችላሉ ወይ?

በመጀመሪያዎቹ የነፃነት ዓመታት ሻዕቢያ የኤርትራዊያንን የዘመናት ጥያቄን መርቶ አሳክቷል የሚል እምነት የነበረውና ለነፃነቱ ቀናኢ የሆነው አብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ ሀብቱን፣ ጉልበቱንና ጊዜውን ለአገር ግንባታና ለኢኮኖሚያዊ እድገት ለማዋል ሙሉ ፈቃደኝነት ነበረው። ይህንን በጐ የሕዝብ መነሳሳት ለአገር ግንባታ ከማዋል ይልቅ ለጠብ ጫሪ ዓላማው መጠቀሚያ ያደረገው ሻዕቢያ ብዙም ሳይቆይ ኤርትራ ከሁሉም ጐረቤቶቿ ጋር የተካረረ ግጭት ውስጥ እንድትገባ አደረገ። ሻዕቢያ ይህንን ሁሉ ሲያደርግ ከኤርትራዊያን ያገኝ ለነበረው ያልተቆጠበ ድጋፍ መሰረቱ የኤርትራዊያንን የነፃነት ትግል ይወክላል በሚል በሕዝቡ ዘንድ የተፈጠረው እምነት እንደነበረ ግልፅ ነው።

ነገር ግን በዚያን ግዜ ከነበረው ሁኔታ ሻዕቢያ የኤርትራን ህዝብ የነፃነት እንቅስቃሴ በመምራት ረገድ ብቸኛው ኃይል እንዳልነበረ መረዳት አያዳግትም። በተመሳሳይም የኤርትራዊያን የነፃነት ጥያቄ ተገቢነት የተገነዘቡ ሌሎች የኤርትራ ተራማጅ ኃይሎች ያደረጉት አስተዋጽኦ ለኤርትራ ነፃነት ስኬት የጎላ ድርሻ እንደነበረው አይካድም።

ከዚህ ሃቅ በተቃራኒ መልኩ ሻዕቢያ ራሱን ለኤርትራ ነፃነት ብቸኛ አስተዋጽኦ አድራጊ በማስመሰል በድህረ ነፃነት ለፈፀማቸው አያሌ ጥፋቶች ኤርትራዊያንን እንደ መረማመጃ ድልድይ ተጠቅሞባቸዋል። የኋላ ኋላ በጊዜ ሂደት በተፈጠረው ግንዛቤ ምክንያት የኤርትራ ህዝብ ሻዕቢያን በጭፍን መደገፍና መከተል አቁሟል። በዚህም ምክንያት በአሁኑ ወቅት ለሻዕቢያ እኩይ ድርጊት መሳሪያ በመሆን ለኢትዮጵያ የደህንነት ስጋት የሚሆኑ ኤርትራዊያን አይኖሩም ማለት ይቻላል። ከዚህ በተቃራኒ በተጨባጭ ሌላ ተልዕኮ ይዘው የሚመጡ ኤርትራዊያን ካሉ ለመመከት የሚችል አስተማማኝ የደህንነት ተቋም ሀገራችን ስለገነባች ሀሳብ ሊገባን አይገባም።

## 2. እውን ኢትዮጵያና ኤርትራ ቴክኒካሊ ጦርነት ላይ ናቸው ወይ?

ይህን አባባል ውስጡን ከፍተን ስናየው የምረዳው ነገር ቢኖር ምንም እንኳ ኢትዮጵያና ኤርትራ በአሁኑ ጊዜ ጦርነት እያደረጉ ባይሆንም በማናቸውም ጊዜ በሁለቱም አገሮች መሀል ጦርነት ማስነሳት የሚችል የስነልቦና፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ወታደራዊ ዝግጅት አለ ብሎ እንደመከራከር ይቆጠራል። የነገሩን ትክክለኛ አለመሆን ለመረዳትም እነዚህን ነጥቦች እያንዳንዳቸውን በመተንተን ለማሳየት እሞክራለሁ።

### የሥነ-ልቦና ዝግጅት

የኤርትራና ኢትዮጵያ ህዝቦች በውጫዊም ሆነ በውስጣዊ ጠላት ምክንያት የጋራ ታሪካቸውን ከግማሽ በላይ የሆነ ጊዜ ጦርነት የተለየው አልነበረም። በዚህም ሳቢያ የጦርነትን አስከፊነትና የሚያስከትለውን ዋጋ ስለሚረዱ የመጨረሻው አማራጭ ካልሆነ በስተቀረ ጦርነትን ለማድረግ የሚያስችል የስነልቦና ተነሳሽነት የላቸውም። በሌላ በኩል በየቀኑ እየከዳ ወደ ተለያዩ ጐረቤት አገሮች በስደተኝነት ከሚጐርፈው ኤርትራዊ ወታደር መረዳት የሚቻለው ነገር ቢኖር ወታደሩ በተደረገው ትርጉም የለሽ ደም አፋሳሽ ጦርነት እንደተሰላቸና ይህንን ለማድረግ በሚያስችል የሥነ-ልቦና አሰተሳሰብ ላይ አለመገኘቱን ነው። በኢትዮጵያ በኩል ምንም እንኳ አገሩን ከወራሪ ለመከላከል እራሱን አሳልፎ የሰጠ የመከላከያ ኃይል ቢኖርም የመንግስትና የህዝብ ዝንባሌና ፍላጐት ልማትና ልማት ብቻ ነው። ስለዚህ ከሁለቱም አገሮች አንፃር ስናየው ለጦርነት ምቹ የሆነ የስነልቦና ዝግጅት የለም። በመሆኑም በሁለቱ አገራት መሀከል የሰላም ድርድር አለመደረጉን ብቻ በማየት አሁንም [ቴክኒካሊ] ጦርነት ላይ ናቸው ብሎ መናገር ይከብዳል።

### የኢኮኖሚ ዝግጅት

ኤርትራ በአሁኑ ወቅት ዳቦ ለመግዛት ወረፋ የያዘ ማለቂያ የሌለው የሰው ሰንሰለት የሚስተዋልባት አገር ሆናለች። ቀድሞውንም ቢሆን የሀገሪቱ አኮኖሚ በውጭ የሚኖሩ የአገሪቱ ዜጐች ለቤተሰቦቻቸው እና ለመንግስት በሚልኩት ገንዘብ ላይ የተመሰረተ ነበር። በአሁኑ ወቅት እነዚህ ዜጐች በሻዕቢያ ላይ በያዙት የተቃውሞ አቋም ምክንያት ወደ አገር ውስጥ የሚልኩትን ገንዘብ በማቋረጣቸው የተነሳ ኢኮኖሚያው ቆሟል ለማለት ይቻላል። ይሄ ብቻ ሳይሆን የኤርትራ መንግሥት ከኢትዮጵያ ያሰባስበው ከነበረው የወደብ ኪራይና ተገቢ ካልሆነ ንግድ ያገኘው የነበረው ጥቅም በመቅረቱም በኢኮኖሚው ላይ ሌላ ተጨማሪ አደጋ ደርሶባታል። በሌላም በኩል የኤርትራ መንግሥት በሚከተለው ጠብጫሪ፣ ሰላም አደፍራሽና አፍቃሪ ሽብርተኛ ፖሊሲ

ምክንያት ሀገሪቱ ለኢኮኖሚ እድገቷ አጋዥ የሆነ እርዳታም ሆነ ብድር ከተቀረው ዓለም ማግኘት አልቻለችም። የእነዚህ ሁሉ ሐቆች ድምር ውጤት የኤርትራን ኢኮኖሚ ጦርነትን ለመሸከም የማያስችል አድርጎታል። በአንፃሩ ምንም እንኳ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚው በፈጣን ሁኔታ እያደገ ቢመጣም የበለጠ ጠንካራ ኢኮኖሚን የመገንባት አስፈላጊነትን የሚረዳ ህዝብና መንግስት ስላለ ኢኮኖሚውን ለጦርነት የማዋል ፍላጐት ጨርሶ የለም ለማለት ይቻላል። ስለዚህ በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል ቴክኒካሊ ጦርነት አለ ለማለት የሚያስችል የኢኮኖሚ ሁኔታ የለም።

## የፖለቲካ ዝግጅት

ኤርትራዊያን ለአገራቸው በነበራቸው በጐ አስተሳሰብ ምክንያት ያላቸውን ነገር ሁሉ ላገራቸው ሁለንተናዊ እድገት ለማዋል ጥረዋል። በዚህም ምክንያት ይመስላል ሻዕቢያ ኤርትራ ከ2 – 3 ሚሊዮን የሚሆን በመላው አለም የተሰራጩ ያልተሾሙ አምባሳደሮች አሏት እያለ በአደባባይ ሲለፍፍ የነበረው። አሁን ግን ሁኔታው ሁሉ ተለውጦ እነዚህ ኤርትራዊያን አገራቸው ከሻዕቢያ በላይ ማንም ጠላት እንደሌላት በመረዳታቸው ሻዕቢያን ከኤርትራ ገፀ ምድር ለማስወገድ በሚደረገው ጥረት ቀንደኛ ተዋናይ መሆን ጀምረዋል። በተመሳሳይም በአለማችን ዛሬ ግጭትን በጦርነት የመፍታት ዘዴን የሚያበረታታ ሁኔታ አለመኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ኤርትራ እየተከተለች ባለችው አደገኛ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ምክንያት በተለያዩ ሀገራት ዘንድ በአይነ ቁራኛ የምትታይ አገር ሆናለች።

በሌላ በኩል ደግሞ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲዋ በኢኮኖሚያዊ ዲፕሎማሲ የተቃኘው ኢትዮጵያ በምትከተለው ትክክለኛ ፖሊሲ ምክንያት በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ዓለም አቀፋዊ አደራን የተቀበለች ሀገር ሆናለች። ስለሆነም ይህንን አዎንታዊ ገፅታዋን የሚያደበዝዝ ጦርነት ውስጥ እንድትገባ የሚያደርጋት ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ የፖለቲካ ግፊት የለም። ለዚህም ነው ኢትዮጵያና ኤርትራ ቴክኒካሊ ጦርነት ላይ ናቸው የሚለው አባባል ከተጨባጭ ሐቁ ጋር ተቃራኒ የሚሆነው።

## ወታደራዊ ዝግጅት

አያሌ የኤርትራ ትውልዶች ለነፃነት የተጋድሎውን ፍትሐዊነት ስለተረዱ ያለስስት እራሳቸውን ሰማዕት አድርገዋል። አሁን ግን በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል የተደረገውን ጦርነት ኢ-ፍትሐዊነትና ኢ-ምክንያታዊነት የተረዱት ኤርትራውያን የመንግሥታቸውን ጦር ጠማሽ ፖሊሲ በመቃወም ድንበር አቋርጠው የጐረቤት አገሮችን የስደተኛ ካምፖች ማጣበብ ከጀመሩ ውለው አድረዋል። በኢትዮጵያ ወገን ዘመናዊና ጠንካራ የመከላከያ ኃይል በመገንባቱ ምክንያት በሀይል ሚዛን ስሌት አንፃር ሲቃኝ ልብን ሞልቶ ጦርነትን አስቀድሞ የሚያስቀር ሁኔታ ተፈጥሯል ለማለት ይቻላል። በጠንካራ ወታደራዊ አቋም ላይ የተገነባው የመከላከያ ሠራዊታችን ሻዕቢያ ጦርነት ላውጅ ብሎ ቢነሳ ውጤቱ እራሱን ማጥፋት መሆኑን በሚገባ እንዲረዳው በማድረጉ የተፈጠረ ሰላም ባይኖርም እንኳ ጦርነት ሳይደረግ እስካሁን ቆይቷል። ስለዚህ ኢትዮጵያና ኤርትራ [ቴክኒካሊ] ጦርነት ላይ ናቸው የሚያስብል ነባራዊ የሆነ ወታደራዊ ሁኔታም የለም።

ስለዚህ ከላይ እንደተጠቀሰው በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል አፍን ሞልቶ ጦርነት አለ ለማለት የሚያስደፍሩ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚያ፣ ወታደራዊ እና የሥነ-ልቦናዊ ዳራዎች (settings) የሉም።

## 3. ኢትዮጵያዊነት የስልጣን ቀበኞች መደበቂያ ዋሻ አይደለም

በኢትዮ-ኤርትሪያ ጦርነት ማግስት በኢህአዴግ ከፍተኛ አመራር አባላት መካከል ጦርነቱን አስመልክቶ የአመለካከት ልዩነት ተከስቶ እንደነበር ይታወሳል። በዚህም ምክንያት በጉዳዩ ላይ የየራሳቸውን አላማ ያነገቡ የተለያዩ ሃሳቦች ተንሸራሽረው አሸናፊው ሃሳብ በድምፅ ብልጫ ስለተለየ ተግባራዊ መሆን ጀመረ። በአንድ ጉዳይ ዙሪያ የተለያዩ ሃሳቦችን የማንሸራሸር ባህል ለነበረው ድርጅት ይህ አዲስ ክስተት አልነበረም። እንዲያውም ይህ በብዙዎች ዘንድ የውስጠ ነፃነቱ ነፀብራቅና ጠንካራ ጐኑ ተደርጎ የሚወሰድና ለማያቋርጥ ጥንካሬውና እስከዛሬም ላስመዘገባቸው ድሎች አይነተኛ አስተዋፅኦ ያለው ድርጅታዊ ፀጋ ተደርጎ ይወሰዳል። ይሁን እንጂ ከዚህ ድርጅታዊ ባህል በተፃራሪ የቆሙ የድርጅቱ ከፍተኛ አመራር አባላት የነበሩ ጥቂት ግለሰቦች የድርጅቱን አንድነት የተፈታተነ የአንጃ ቡድን መሠረቱ። የእራስን ስብእና አግዝፎ የማየት አባዜ የተጠናወተው ይህ ቡድን ለድርጅቱ ደንብና ሥርዓት እራሴን አላስገዛም በማለት የተፈጠረውን ልዩነት "ከአገር ሉአላዊነት" ጋር የተያያዘ በማስመሰል የኢትዮጵያ ህዝብ ለሉአላዊነቱ ያለውን ቀናኢነት ለጠባብ ቡድናዊ ጥቅሙ ማራመጃነት ይጠቀምበት ጀመር።

በመሠረቱ የዚህ ቡድን አቋም ስህተተኛነት የሚያስረዱ ብዙ የታሪክ ማስረጃዎችን ማጣቀስ ይቻላል። አንደኛው ማሳያ የድርጅቱን መራር ትግል በግንባር ቀደምትነት ትግሉን የመሩና 2/3ኛ የወጣትነት ዕድሜያቸውንና ትምህርታቸውን ለዚህ ክቡር አላማ ሲባል መስዋእት ያደረጉ የመሪዎችን ሚና አሳንሶ በማቅረብ የራሳቸውን [የአንጃውን መሪዎች] ሚና አግዝፎ በማሳየት በልምሹ አቋማቸው ዙሪያ ሰፊ የሕዝብ ድጋፍ ለማሰባሰብ ከንቱ ጥረት አደረጉ። ከሙስናና ከሥልጣን ብልግና ጋር የተያያዘውን የልዩነት ነጥብ ማዛባትና አውገርግሮ ማቅረብንም ሥራዬ ብለው ተያያዙት። ብቻቸውን የተወጉት የኢትዮጵያዊነት መርፌ ያለ ይመስል ለራስ በተሰጠ ከእኔ በላይ ኢትዮጵያዊነት ላሳር የሚል (self proclaimed) ኢትዮጵያዊነት ከእኔ በላይ ፋከራም ወደ ተራ አተካራ የሚያመራ የዘቀጠ አስተሳሰብ ውስጥ ተዘፈቁ። የነገብሩ እስራት ከትግል መውጣት መሰረቱ የወቅቱ የትግል መድረክ የሚጠይቀውን እውቀትና ምክንያታዊነትን መሰረት ያደረገ የአመራርነት ሚና መጫወት አለመቻል ነው። ይህ የአመራር ብቃት ማነስም ከግለሰብ አልፎ ወደ ፓርቲ ደረጃ በማደጉ አጠቃላይ የሆነ መቆም ሲከሰት ጉዳዩ ያሳሰበው አካል የህይወት አድን እርምጃ በመውሰድ ፓርቲውን ከጥፋት ታድጓል። መጀመሪያውኑም በወቅቱ ለተፈጠረው ልዩነት ምክንያት ኢህአዴግ እንደ ድርጅት ሚዛናዊ የሆነ ፍርድ ከህዝቡ እንጂ ከእንዲህ ዓይነቶቹ ተንጠባጣቢዎች ስለማይጠብቅ ወቀሳቸው አንዳችም ፋይዳ ስለማይኖረው አያስገርመኝም።

ወታደራዊ ድል ወደ ሌላ ትልቅ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ዲፕሎማሲያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ስኬት የሚመራ ድል እንጂ በራሱ ግብ የሆነ (self evident) ልክ እንደ ቦክስ ውድድር በመጋጠሚያው ሜዳ ተጋድሎ ብቻ የሚወሰን ጉዳይ አይደለም። ይልቁንስ ውስብስብና አለም አቀፋዊ የሆኑ የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚና የዲፕሎማሲ

ጉዳዩችን የሚነካ ግዙፍ ጉዳይ እንጂ። ስለዚህ ከሌሎች ልዩነቶች በተጨማሪ በኢህአዴግ አመራር መካከል የተፈጠረው ይህ ልዩነትም ጦርነትን ማሸነፍ በራሱ ግብ አድርጐ መውሰድና ጦርነትን ከጠባብ ትርጉሙ በሰፋ መልኩ በማየት መካከል ነው። የተፈጠረው ልዩነትም ይህንን በመገንዘብና ባለመገንዘብ መካከል ነበር። ስለዚህ የዚህን መመሪያ መውጣት በተለያየ መድረክ እያሰሙት ለነበረው ክስ ማስረጃ አድርጐ ለማሳየት መሯሯጥ የማየዋጣ ተግባር ነው። ለህጉ መውጣት ምክንያት የሆኑት ጉዳዮች በህጉ መግቢያ ላይ ማግኘት ይቻላል። በህጉ መግቢያ ላይም እንደ ተጠቀሰው ይህ ህግ በኤርትራ መንግስት ላይ የተከፈተው ዘርፈ ብዙ የሆነው የማዳከሚያ ስልት ተቀጥላ ብቻ ነው።

## 4. በደንቡ የተቀመጡት (ለደህንነት ስጋት የሆኑ ኤርትራዊያን አይገቡም የተባለው ዓይነቶቹ) ለይስሙላ የገቡና ለአተገባበር አመቺ አይደሉም ስለተባለው

በመጀመሪያ አንድ ህግ ሲወጣ መሰረት የሚያደርገው በሀሳብ ላይ የተንጠለጠለ አቅምን ሳይሆን በተጨባጭ የመፈፀም አቅምን (Reflexive equilibrium) ነው። ስለዚህ በህጉ መውጣት ሳቢያ ሊከተሉ የሚችሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ከላይ የተጠቀሱትን ክልከላዎች በማበጀት ለማስቀረት ሲሞክር ይህንን ክልከላ ለማስፈፀም የሚያስችል ተቋማዊ አቅም በተጨባጭ ላይ መኖሩንም ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው።

ከዚህ አንፃር ስናየው በእርግጥ የጉዳዩ ባለቤት የሆነው የደህንነት ተቋም ይህንን ጉዳይ በተገቢው መልኩ ሊወጣው ይችላል ወይ የሚለውን ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ይሆናል። በአሁኑ ሰዓት ከአስመራ እስከ ሞቃዲሾ በተዘረጋ የጥፋት ሰንሰለት ኢትዮጵያን ለማሸበር ሻዕቢያ መራሽ በሆኑ የተለያዩ ኃይሎች እየተሯሯጡ ይገኛሉ። በተመሳሳይም ህጋዊና ሰላማዊ የፖለቲካ ገበያው የተፋቸው ግለሰቦች የቀቢፀ ተስፋ እርምጃን ለመውሰድ ሲዳክሩ ይገኛሉ። የሚገርመው ግን እነዚህ ሁሉ የጥፋት ጥረቶች ቢኖሩም በአገሪቱ ውስጥ አንዳችም አደጋ አለመከሰቱ ነው። ለዚህ ስኬት የተለያዩ አካሎች የየራሳቸውን በጐ አስተዋጽኦ ቢያደርጉም የብሔራዊ ደህንነት አገልግሎት የአንበሳ ድርሻ ይወስዳል። ይህ ተጨባጭ አቅም ባለበት ሁኔታ በመመሪያው የተካተቱት የጥንቃቄ ድንጋጌዎች መፈፀም አይችሉም ብሎ መናገር አንድም የደህንነት ተቁሞቻችን አቅም ካለመረዳት አሊያም ሆን ብሎ ላለመረዳት ከሞመከር በስተቀረ ተገቢ ስጋትን ያነገበ አስተያየተ አይደለም።

## 5. በመመሪያው መውጣት ምክንያት ሊፈጠር የሚችለው የኢንቨስትመ ንት ፍሰትና የስራ እድል፤

የመመሪያውን መውጣት አስመልክቶ ከተሰነዘሩ ሃሳቦች መካከል ኤርትራዊያን በአገሪቱ የስራ ገበያ ውስጥ እንዲሳተፉ ስለሚያደርግ ኢትዮጵያውያን ለሆኑ ዜጐች የስራ እድልን ያጠባል የሚል ነው። በመሰረቱ ደንቡ የሚደነገገው ኤርትራዊያን በኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቬስት ማድረግ ስለሚችሉበት ሁኔታ ነው። ይህ ደግሞ በሕጉ መውጣት ምክንያት በሚመጣው ተጨማሪ የመዋለ ነዋይ ፍሰት የተነሳ አገራችን በውጭ ምንዛሬ ፍሰት መጨመር፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር እና በተጨማሪ የሥራ ዕድል ተጠቃሚ ከመሆኗ በስተቀር ሌላ ጉጂ የሆነ ተጨባጭ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖ አይደርስባትም።

በተመሳሳይም በአገሪቱ ሕገ-መንግስት እንደተጠቀሰው የውጭ ባለሃብቶች በህግ በተደነገገው መሠረት ወይንም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ካልሆነ በስተቀረ በኢትዮጵያ ውሰጥ ለሚያፈሱት ሃብት በቂ የሆነ ጥበቃ ይደርግላቸዋል። የዚህ ህግ መውጣት ደግሞ ይህንን መርህ ከማስፈፀምና ለውጭ ባለሃብቶች ተገቢውን ጥበቃ ከመስጠት አንፃር የማይናቅ ሚና ይጫወታል። በዚህም ምክንያት ለውጭ ኢንቬስተሮች ዋስትና ከመስጠት አንፃር የዚህ ሕግ መውጣት የሀገራችንን ገፅታ አንድ እርምጃ ወደፊት ያራምደዋል።

---END---